# የተጀመረው የመተካካት ስርዓትን ማጠናከር ለዘላቂ ልማት ወሳኝ ነው!

**ተስፋየ ለማ**

በአገራችን የመተካካት ስርዓት ይፋ በተደረገበት ወቅት የተለያዩ ክፍሎች የፈጠረባቸውን ስሜት በተለያየ መልክ አቅርበው ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር መተካካት በአገሪቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ላይ የጎላ ሚና ስላለው ቀደም ሲልም በድርጅቱ ሲፈጽመው እንደነበር በማስገንዘብ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር እቅድ መንደፉን በማያሻማ መንገድ ያቀረበ ቢሆንም ብዙዎች ዘንድ እምነት ማሳደር አልቻለም ነበር። አፈጻጸም ላይ ችግር ያጋጥመዋል የሚል ብዥታም ፈጥሮ ነበር።

ይሁንና በ2000 ዓ/ም የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ በኢህአዴግና በአባል ድርጅቶቹ የአመራር መተካካቱ በጎላ መልክ የታየበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። በብአዴን፣ በህወሓት፣ በዲኢህዴንና በኦህዴድ የአመራር መተካካቶች ተካሂደዋል። ከዚያም አልፎ በፌዴራል የመንግስት ከፍተኛ የስልጣን እርከኖች ላይ የተደረገው መተካካት ቀላል አልነበረም።

ነባር ታጋይና የትግል መስራቾች ከነበሩት መካከል ታጋይ አዲሱ ለገሰ፣ ታጋይ ስዩም መስፍን፣ ታጋይ ዋልዋ ተፈራና ሌሎችም በሌሎች አዳዲስ አመራሮች መተካታቸው የሚታወቅ ነው። በዚያን የከፍተኛ የመንግስት አመራር መተካካት አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ታጋይ አዲሱንና ታጋይ ስዩምን እንዲተኩ መደረጉ ይታወቃል። እንደዚሁም አቶ ደመቀ መኮንን የብአዴን ሊቀመንበር ሆነው ሲመረጡ አቶ አባይ ወልዱ ደግሞ የትግራይ ርዕሰ መስተዳድር ሆነው መተካታቸው ይታወቃል።

ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ግን በመተካካቱ ዙሪያ የጠራ የሃሳብ ልዕልና በህዝብ ዘንድ የሰረጸበት ሁኔታ አልነበረም። ተሞክሮው በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ በመሆኑ የተፈጠረውን ዴሞክራሲያዊ አሰራር ተቀብሎ ከማገዝና አፈጻጸሙን በጋራ ከመስራት ይልቅ በጥርጣሬ ውስጥ የገባው የሰው ቁጥር ቀላል አልነበረም።

ይህ የሆነበት አንድም በአገራችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ያልተለመደ በመሆኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአገራችን ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት እንዲሰፍን የማይሹ አካላትና የኢትዮጵያ ጠላቶች በሚያራግቡት አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ በመታለል ነበር።

በመሆኑም በሰለጠነ መንገድ ነባር አመራር ለወጣቱ ትውልድ እያስረከበ የአገሪቱን ሁለንተናዊ ገጽታ መቀየር የሚያስችል የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ተግባራትን የመፈጸሙ ጉዳይ ተግባራዊ

ይሆናል ብሎ በእምነት ለመቀበል አስቸጋሪ ተደርጎ የተወሰደበት ሁኔታ ቢኖርም በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ አመራር በየደረጃው የመተካካቱ ስርዓቱ በተገቢው መንገድ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ መስከረም 11 ቀን 2005 ዓ/ም በአገሪቱ የመጨረሻው ከፍተኛ የስልጣን እርከን የመተካካቱ ስርዓት ተፈጽሟል።

መስከረም 11 ቀን 2005 ዓ/ም በኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተባት እለት ሆና በኢትዮጵያ የታሪክ ማሕደር መመዝገብ ቻለች። በኢህአዴግ ቀደም ሲል የተነደፈውና በየደረጃው ሲከወን የመጣው የመተካካት ስርዓት በአገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን እርከን የጠቅላይ ሚኒስትርንና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ቦታዎችን የመተካካት ስርዓት በተገቢው መንገድ ተከናወነ።

ኢህአዴግ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ፈጠረ። በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማትን ከማስፈን ጎንለጎን በሌሎች ዘንድ እምነት መፍጠር ባይችልም የመተካካት ስርዓቱን ለማስቀጠል ጠንክሮ እየሥራ መምጣቱን ያስመሰከረለት ያለምንም ልዩነት አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ መተካት ችሏል።

በታጋይ መለስ ዜናዊ አመራር ኢህአዴግ አገሪቱ ተዘፍቃ ከነበረበት የኋላቀርነትና የድህነት ማጥ ለማላቀቅ ድህነትን መዋጋት ቀዳሚ አጀንዳ አድርጎ በመውሰድ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በዘላቂነት ማሳደግ የሚያስችል የልማት አቅጣጫን በመከተል ድህነትን ታሪክ ማድረግና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ የሚያስችል አስተማማኝ መሰረት ገንብቷል።

ባለፉት ዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት ሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ እየተመዘገበ ያለውን እድገት የላይኛው ጫፍ ለማድረስ የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተነድፎ ከሁለት ዓመት በፊት ተጀምሮ ትግበራ ላይ ይገኛል። በቀጣይ ሶስት አመታት በሚኖረው የተጠናከረ የአፈጻጸም ብቃት አገሪቱን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ እንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል መሰረት ይገነባል የሚል እምነት ተይዟል።

የኢኮኖሚ እድገቱን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን የስርዓቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ በአገራችን የልማታዊ ዴሞክራሲ ስርዓትን በአስተማማኝ መልክ ለማስረጽ ያላሳለሰ ተግባራትን ፈጽሟል። በተለይ ወጣቶችን በመመልመልና የስርዓቱ አስቀጣይ ሃይል እንዲሆኑ በማድረግ ረገድም ቀላል የማይባል ሥራ ተከናውኗል።

አዲሱ ትውልድ ነባሩን አመራር እየተካ የአገራችንን እድገት ባልተቆራረጠ መልኩ ለማስቀጠል የሚቻልበት አሰራርም ተዘርግቷል። የመተካካት ስርዓቱ ተግባራዊነት ወሳኝ እንደሆነ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመናቸው ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለኢህአዴግ

አባላት ያስጨበጡት መርህ ነበር። ከመርህነት አልፎ በህይወት በነበሩበት ዘመን የመተካካት ስርዓቱ አፈጻጸም ዝርዝር ተነድፎ በየደረጃው ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመናቸው ለአንድ የውጭ ሚዲያ በሰጡት ቃለምልልስ ድርጅታቸው በትግል ሜዳ ያልነበሩ ሲቪል አመራሮችን በማፍራትና ከነባር አመራሮች ተሞክሮ እየቀሰሙና ከነባራዊ ሁኔታው ጋር እያቀናጁ የአገሪቱን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ማስቀጠል የሚቻልበት አሰራር መዘርጋቱን ገልጸው ነበር። ቀስበቀስ አዳዲስ ወጣት አመራሮች ነባሮቹን እየተኩ የሚመጡበት አሰራር መዘርጋቱን አስረድተው ነበር። በመጀመሪያው ረድፍ የተተኩት ከፍተኛ አመራሮችም ከዚህ አንጻር እንደነበር መግለጻቸው ይታወቃል።

ይሁንና ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሐምሌ ወር 2004 ዓ/ም በድንገት በማረፋቸው የተነሳ የኢህአዴግ አመራሮች ለስልጣን ሲሉ እርስ በርስ ይባላሉ፣ አገሪቱ መቋጫ ወደሌለው ብጥብጥና ሁከት ትገባለች፤ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ አበቃላት የሚሉና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ዘገባዎች በተለያዩ ተንታኞችና ሚዲያዎች ተስተጋብተዋል።

አቶ መለስ ዜናዊን ሊተካ የሚችል ስለሌለ ኢህአዴግ አበቃላት ያሉም ነበሩ። ነባር ታጋዮች ስልጣኑን አሳልፈው ለአዲስ አመራር አይሰጡም እነሱም ቢሆኑ በብሄር ተከፋፍለው ሁከት ይፈጥራሉ በሚልም የተማረተው ቀላል አልነበረም።

በኢህአዴግ አመራሮች ላይ የስልጣን ሽኩቻ ይፈጠራል የአገሪቱ ሰላምም ይደፈርሳል በሚል ይነሳ የነበረው ኢህአዴግን ባለማወቅ አለበለዚያም ሆን ተብሎ የአገራችንን ሰላም ለማደፍረስ እንደሆነ አሁን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግሃድ ሆኗል።

ታለቁ መሪ በህይወት ዘመናቸው ያሰረጹት የአሰራር ስርዓትም አደራ የተሸከመው ነባሩ የኢህአዴግ አመራር ተግባራዊ ለማድረግ አላቅማማም። በአገሪቱ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርና መተካካት ተግባራዊ እስካልተደረገ ድረስ እስካሁን የተመዘገበውን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ስኬትንና የልማታዊ ዴሞክራሲ ስርዓትን በተገቢው ደረጃ መርቶ ዳር ማድረስ እንደማይቻል የተገነዘቡት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በህይወት ዘመናቸው ሲናገሩ "የእኛ ሩጫ በአንድ ሜዳ ሮጠን የሚናሸንፍበት የማራቶን ሩጫ አይነት አይደለም። የእኛ ሩጫ የዱላ ቅብብሎሽ ሩጫ ነው። አንዱ ለአንዱ እያቀበለ የመጨረሻ ውጤት የሚገኝበት ሩጫ።" በማለት ነበር የሚገልጹት። እውነትም በአንድ ትውልድ የሚያልቅ አለመሆኑን የተገነዘበው የኢህአዴግ አመራርም የመተካካቱን ስርዓት በተገቢው ሁኔታ እያስፈጸመ ይገኛል።

በአገራችን የተጀመረው ጸረ ድህነት ዘመቻ፣ በአገራችን የተጀመረው ሰላምንና ዴሞክራሲን የማስፈን ጥረት ለማስቀጠል አንድ ትውልድ የቻለውን ያህል ሰርቶ ዳር አድርሶት በዚያ የሚያቆም

አይደለም። ይልቁንስ አንድ ትውልድ ከደረሰበት ሌላው በመቀበል የቻለውን ያህል ደረጃ ላይ አድርሶ እንደገና ለተተኪው ትውልድ በማስረከብ ነው የአገራችን ልዕልና በዘላቂነት ተረጋግጦ ከትውልድ ትውልድ እንደተጠበቀ ሊኖር የሚችለው።

በርካታ የፖለቲካ ሳይንስ ተንታኞች በኢትዮጵያ የመተካካት ስርዓቱ ተግባራዊ አይሆንም የሚል እምነት ነበራቸው። ይህንኑ እምነታቸውም በተለያዩ ዓለምአቀፍ ሚዲያዎች የሚያስተጋቡበት ሁኔታ ነበር። የዚህ እምነት ተጋሪ የሆኑ ዜጎች ቁጥርም ቀላል አልነበረም። የመተካካት ስርዓቱ በትክክል እንደሚካሄድ የሚያውቁት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ግን በተለያየ አጋጣሚ ተግባራዊ እንደሚሆን ይገልጹ ነበር። የመተካካቱ ተግባር ይፈጸማል የሚል እምነት መያዝ የቻሉት የድርጅቱን ታሪክ በሚገባ ስለሚያውቁና በአገራችን የተመሰረተው ስርዓት ቀደምት አራማጅ ከመሆናቸውም ባሻገር የድርጅቱ የውስጥ አደራጀትና አሰራር ለሽኩቻና ለአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት ክፍተት የማሰጥ መሆኑን በመገንዘብ ነበር። ይህ ሁኔታ በተለያዩ የኢህአዴግ አባላት ቢነገርም ብዙም ትኩረት የሰጠው አልነበረም። የመተካካት ስርዓቱ አይተገበርም የሚለው ሃሳብ ሚዛን ይደፉ እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ዜሬ ግን ሁኔታው ተቀያይሯል። በኢህአዴግ ቀደም ብሎ የተወጠነውና በመካከለኛና በከፍተኛ አመራሮች ላይ ሲተገበር የነበረው የመተካካት ስርዓት በከፍተኛው የስልጣን እርከን ተከናውኗል። ኢህአዴግ ለምን እንደታገለም በተጨባጭ አስመስክሯል። የኢትዮጵያን ህዝብ ከአምባገነኑ ሰው በላው ስርዓት ለማላቀቅና በአገሪቱ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን እንደሆነ በተጨባጭ ታይቷል። አገሪቱን ከተመጽዋችነት ለማላቀቅና ህዝቧን መመገብ የምትችል፣ ለሌለች የአፍሪካ አገሮች መመኪያና ከለላ የሚትሆን አስተማማኝ ኢኮኖሚ ያላት የተረጋጋች አገር እንዲትሆን ለማስቻል እንደነበር ሁሉም የሚመሰክረው ነገር ሆኗል። ይህ ደግሞ እስካሁን በተከናወኑ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ተግባራት እየተረጋገጠ የመጣበት ሁኔታ ታይቷል ዛሬ ደግሞ ከሁሉም የላቀው የመተካካት ስርዓት በአገራችን እውን ሆኗል።

በኢትዮጵያ ስልጣን በአፈሙዝ መያዝ ካከተመለት ሃያ ዓመት ተቆጥሯል። የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ባለቤትነት ተረጋግጧል። ወደ ስልጣን የሚወጣ ማንኛውም አካል ህዝብን ለማገልገል እንጂ በህዝብ ለመገልገል እንዳልሆነ በህዝቡ ሆነ በፖለቲከኞች ዘንድ ሰርጿል። ህዝቡ ያስተዳድረኛል አገሪቱን ወደተሻለ ደረጃ ያደርሳል ያለውን የፖለቲካ ድርጅት በፍትሃዊነትና በነጻነት መምረጥ የሚችልበት አስተማማኝ ስርዓት ተገንብቷል።

በህዝብ ምርጫ ወደስልጣን የመጣው የኢህአዴግ ድርጅትም የያዘውን ራዕይ ዘለቄታ እንዲኖረው ለወጣቱ ትውልድ እያስረከበ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የድርጅቱን በርካታ ከፍተኛ የአመራር ቦታዎችን ያያዙት ተተኪ ወጣቶች ሆነዋል። ቀደም ሲል አቶ አዲሱ ለገሰ የኢህአዴግ ነባር ታጋይና በኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲያገለግሉ የነበሩ፣ ብአዴንን በሊቀመንበርነት

የመሩ ህይወታቸውን ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳልፈው ከሰጡ ታላላቅ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች አንዱ የሆኑት በድርጅታቸው በአቶ ደመቀ መኮንን ሲተኩ በፌዴራል መንግስት የነበራቸው ሃላፊነት ደግሞ በአቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ መተካታቸው ይታወቃል።

መስከረም 11 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገው መተካካት ደግሞ አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝን ጠቅላይ ሚነስትር ያስደረገ ሲሆን አቶ ደመቀ መኮንን ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒትር ሆነዋል። ሁለቱም ጓዶች የላቀ የፖለቲካና የአመራር ብስለት እንዳላቸውም በርካቶች ይመሰክራሉ።

ኢህአዴግ ለምን አቶ ሃይለማሪያምን ለእጩ ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዳቀረበ የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበርና የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በገለጹበት ወቅት ቀደም ሲል የተጀመረው የመተካካት መርህ መሰረት በማድረግና የአሰራር ደንቡ በሚፈቅደው ሆኖ አቶ ሃይለማሪያም ከታላቁ መሪ ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቅርበት ልምድ መቅሰማቸውን ገልጸዋል።

አቶ ደመቀ አያይዘውም አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ በእንጂነሪንግና በአመራር ሳይንስ ሁለተኛ ድግሪ እንዳላቸው አስታውሰው ከዩኒቨርስቲ ዲንነት እስከ ከፍተኛ የመንግስት የሃላፊነት ቦታ ሲያገለግሉ እንደነበር ገልጸዋል።

ከ47 ዓመታት በፊት በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ቦሎሶ ሶሬ ወረዳ በአረካ ከተማ የተወለዱት አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ በ1980 ዓ/ም የባችለር ድግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በምህንድስና እንዳገኙ ይታወቃል።

በወጣትነት ዘመናቸውም በአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በመምህርነት አገልግለዋል። በፊንላንድ በማቅናት ከታምፔሬ የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በስነ ንፅህና ምህንድስና የማስተርስ ድግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን የእውቀት አድማሳቸውን ለማስፋት ባደረጉት ጥረትም ከአሜሪካው አዙሳ ፓስፊክ ዩኒቨርሲቲ በድርጅት አመራር የማስተርስ ድግሪ አግኝተዋል።

በ1990ዎቹ መግቢያ ላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ አባል በመሆን ተሳትፎ በመጀመር የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስትን ምክትል ርእሰ መስተዳደር ሆነው ካገለገሉ በኋላ ከ1998 ጀምሮ ለአራት ዓመታት የክልሉ ርእሰ መስተዳድር ሆነው ሰርተዋል። ከዚያም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ጉዳዮች ተጠሪ ሚኒስትር ሆነው የሰሩ ሲሆን በተጓዳኝም በጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አማካሪ ሆነው መስራታቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በ2002 አገር አቀፍ ምርጫ በኋላም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነትና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ተሹመው በማገልገል ላይ ነበሩ።

መስከረም 11 ቀን 2004 ዓ/ም የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ቃለመሃላ የፈጸሙ ሲሆን ከቃለመሃላ በኋላ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ራዕይ ዳር ለማድረስ ጠንክረን እንሰራለን፤ በአገራችን በታላቁ መሪ የተጀመሩትን የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ተግባራት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አያይዘውም የታላቁ መሪ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ጅምር የሆነው የአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አካል የታላቁ ህዳሴ ግድ በታቀደለት ጊዜ ከተቻለም ከዚያ ባነሰ ወቅት ለማጠናቀቅ ርብርብ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

አርሶና አርብቶ አደሩ ዘመናዊ የእርሻ አመራረት ዘዴ ተጠቃሚ እንዲሆንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል አሰራር እንዲከተል እየተደረገ ያለው የግብርና መር የልማት እንቅስቃሴም እንደሚጠናከር የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለይ ለልማታችን እንቅፋት የሚሆነውን የኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን በተቀናጀ መንገድ በመታገል ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈጣን አሰራር ይዘረጋል ብለዋል።

እንደዚሁም በትምህርት ዘርፍ ለሳይንስና ለሂሳብ ትምህርቶች ትኩረት እንደሚሰጥ ጠቁመው የእናቶችንና የህጻናትን ሞት ለመቀነስ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ። የወጣቶች እምቅ አቅም የአገራችን ተስፋ ስለሆነ የወጣቱ ተሳትፎ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሴቶች ተሳትፎም በሁለንተናዊ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና እንዲጎለብት እናደርጋለን ብለዋል።

ኢህአዴግ ቀደም ሲል የጀመረውን የመተካካት ስትራቴጂ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ በማድረግ በአገራችን የተጀመረው የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት እቅዶችን እውን ለማድረግ የሚያስችለው መንገድ እየተከተለ መሆኑ እሙን ከምግዜው በላቀ መንገድ በያዝነው ወቅት ግሃድ ሆኗል። ይህ የመተካካት ተግባር የአገራችንን ህልውና ከማረጋገጡም በላይ የህዝቧን ብልጽግና በቀጣይነት እንደሚያረጋግጥ ይታመናል። ኢህአዴግ ከመጀመሪያ አንስቶ አንግቦት የተነሳው የአገራችን ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት የማረጋገጥና የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትን ጠብቆ የአዲስቷን ኢትዮጵያ ህዳሴ የማረጋገጥ እንደዚሁም በአገሪቱ ፍትሃዊነት የማስፈን ዓላማ እውን እየሆነ መጥቷል በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል።